# ትግላችን

**ትችት! በዱጋ ሒማ፤**

**ክፍል ፩፤ ከገጽ ፯ እስከ ገጽ 33።**

***፩ኛ/ የአሳታሚው ማስታወሻ***

አሳታሚው በማስታወሻቸው፤ *"ኮሎኔል መንግሥቱ በሥልጣን ላይ ሳሉ የመሩት አብዮት ስላካሔደው ትግል እራሳቸው እንደሚያስታውሱት ሲያካፍሉን የመጀመሪያው ርዕሰ ብሔር ይሆናሉ፤"* ብለዋል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለመነኮሳቷ ካዘጋጀቻቸው መጻሕፍቷ አንዱ የሆነው ማር ይስሐቅ እንዲህ ይላል፤ **"መሐይምነት ለድፍረት፤ ፍቅረ ንዋይ ለከኽደት ይመቻል።"** አሳታሚና አርታኢው ኤልያስ ወንድሙ ከነዚህ ድክመቶች ቢያንስ በአንዱ ተቀፍድደዋል። ምክንያቱም አጼ ኃይለ ሥላሴ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ በሚል ርዕስ ሁለት ቅጽ መጻሕፍት አሳትመው አስነብበውናል። ለዚያውም የመጀመሪያውን እንደ ኮሎኔል መንግሥቱ በስደት በነበሩ ወቅት ምንም ዓይነት መረጃ ከማንም ሳይሹ።

አርታኢው እነዚህን መጻሕፍት ካላነበቧቸው፤ የኮሎኔል መንግሥቱን መጽሐፍ አስተካክሎና አርሞ ለኛ ለማቅረብ የሚያስችል የአእምሮ ብቃት አይኖራቸውም። የኮሎኔል መንግሥቱ ታሪክ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ የቀጠለ ነውና ሊያነብቡት ግድ ነበር። አለበለዚያ እንደዘመኑ ቋንቋ ጉዳዩ ቢዝነስ [የሸፍጥ ንግድ] ከሆነ፤ ሰጎን ልትደበቅ ጭንቅላቷን ከአሸዋ እንደምትቀብር ሐቅን ሊቀብሩ ሲጥሩ ተይዘዋል።

በነገራችን ላይ መንግሥቱ አብዮት አልመሩም፤ አብዮቱን የመራው ሕዝብ ነው፤ እርሳቸው የሕዝቡን አብዮት በጠመንጃ ነጠቁ። ተነጠቅን ብለው ደፍረው የተቃወሙትን ገድለው፤ አስከሬናቸውን ሸጡ። አርታኢ ኤልያስ ይኽ ጠፍቶዎት ይሆንን? መልሱን ለኅሊናዎ እተዋለሁ።

***፪ኛ/ መቅድም***

*"ኢትዮጵያውያን ከያኒያንና የታሪክ ምሁራን ስለአገራችን ለመጻፍ ሲሞክሩ መረጃዎችንና የታሪክ ዋቢዎችን ፍለጋ በአውሮፓና በአረብ አገሮች መዟዟርን ማዘውተራቸው ከሚያሳዝነን በላይ የራሳችንን ታሪክ ከባዕዳን መስማትና መማር ለመሸከም የሚያዳግት የሃፍረት ጫና ሆኖ ኖሯል። እስካሁንም አልተቃለለም።"* ይደንቃል!!! ያንኪ የተጎለጎለበትን የታሪክ ልቃቂት መልክ ለማስያዝ ከኛ ዘንድ ይሮጣል፤ የኛዎቹ ቀላዋጮች እዚያ ይማስናሉ። በመጀመሪያ ምሁር መረጃ አይፈልግም፤ ምናልባት ራስዎን ምሁር ነኝ ብለው ከሆነ መዝገበ ቃላት እናውስዎና ከዚያ በኋላ የሚሆኑትን ይሁኑ።

ኢትዮጵያ ስንኳንስ የራሷን፤ የእስራኤሎችን ታሪክ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ አቆይታ አስረክባቸዋለች። ኢትዮጵያ የየትኛውንም የህልውናዋን ዘመን ታሪክ፤ ሰነድ አጉድላ የምታውቅ ሐገር እንዳልሆነችና እስከ ምጽአትም የማይጎድልባት እንደሆነች እኔ መሐይሙ ምስክር ነኝ። ማረጋገጥ ከፈለጉ የቸገረዎን ይጠይቁና ምላሽ ቢያጡ እኔ ልቀጣ [በለመዱት ይቅጡኝ]፤ ምናልባት ምላሹ ሰምተውት የማያውቁት ወይንም መስማት የማይሹት ሐቅ እንዳይሆንብዎ እሰጋለሁ። እርስዎ በአናቱ መለዮ ያልደፋ ወይንም አንገቱን በጨርቅ ያላነቀን መች ከሰው ይቆጥሩትና እንጂ።

*"... አንድ ሀቀኛ አብዮት ተግባሩ መሆን ያለበት ታሪክን መሥራት እንጂ የራሱን ታሪክ መጻፍ አይደለም በማለት የተዘጋጀው ረቂቅ በቤተ-መዘክር እንዲቆይ ባንወስን ኖሮ ይህ ትግላችን የተሰኘ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ታሪክ የመጀመሪያው ክፍል ብቻ ሳይሆን ምናልባትም ተከታታዮቹ ጭምር ባለፉት ሀያ ዓመታቶች ውስጥ ተጽፈው ለሕዝብ በቀረቡ ነበር።"* ሰደፍ እያሳያችሁ ያጻፋችኋቸውን ነዋ ዛሬ "ከቤተ-መዘክር" [ወመዘክር] በተካኑበት ስርቆት አስወጥተው ካላነበባችሁ የሚሉን። በአርታኢ ኤልያስ ተቀባብቶ የቀረበልን ሸፋኑ እንጂ ውስጡ የርስዎ አይደለማ።

ለነገሩ መንግሥቱ መጽሐፍ ሊያሳትሙ ነው ብለው ትዝታቸውን የጻፉላቸው ሲያስነብቡን ምን ዓይነት ሊሆን እንደሚችል መገመት አዳግቶኝ ነበር። የአሳማ ደም በጠርሙስ ሞልቶ በአደባባይ የሚወረውር አእምሮ፣ ካስትሮ መስቀል አደባባይ አበባ ያቀረበችላቸውን ልጃገረድ ከንፈር ሲስሙ እኔስ ከማን አንሼ ብሎ የሳመ ስስታም፣ ስንኳንስ ሰው ትንኝ አልገደልኩም ብሎ የዋሸ ኅሊና፣ "አማ ማለት" እያለ የሌለ እብራይስጥ ፈጥሮ በድፍረት የተናገረ፣ ጎማ አስተንፍሰናል እናስተነፍሳለንም ብሎ በጎማ

የአገር አስተዳደርን የሚመስስል፤ ምን ሊጽፍ እንደሚችል መገመት እንኳን በዕውን፤ ተኝተው ሌት እንቅልፍ ይነሳል።

*"ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት በአሥራ ሰባት ዓመታት ውስጥ ያከናወናቸውን አያሌ ዲሞክራሲያዊ ተግባሮችና የኢትዮጵያ ሕዝብ የተቀዳጃቸውን ድሎች ሁሉ ለጊዜው ወደጎን በመተው፤ ከብዙ ሺህ ዓመታት ወደ ኋላ ጎታችና ጨቋኝ ጉልታዊ ሥርዓተ ማህበር የተላቀቀበትና የሪፐብሊክ መንግሥት ምስረታውን ብቻ ብንመለከት፤ ጠላቱንና ወገኑን በውል ለይቶ የሚያውቅ፤ የሚጎዳውንና የሚጠቅመውን የሚገነዘብ፤ የነቃና ውለታ የሚገባው ሕዝብ በአገራችን በሚፈጠርበት ጊዜ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት በኢትዮጵያ ታሪክ ያለወደር ተንፈራጦ በተከታታይ ትውልዶች ህሊና ለዘላለም የአብዮት እንቁ ሆኖ ሲያበራ ይኖራል።"* ጓድ መንግሥቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቱንና ወገኑን በሚገባ የሚያውቅ፣ ውለታ የማይዘንጋ፣ ከየትኛውም ዓለም ሕዝብ የነቃ ሕዝብ ነው፤ ለዚህ ምስከር ቢፈልጉ በተለያዩ ዘመናት ያሉ የአዝማሪዎችን ግጥም ያንብቡ። ታሪክ ደግሞ ዕውነት እንጂ ምኞት እኮ አይደለም፤ ገና ለሚወለድ ትውልድ ነበራ ሲመትሩን የኖሩት፤ ለነገሩ ዕውነትዎን ነው እርስዎን በሥልጣን ላይ ያፈናጠጡት አንድ ትውልድ እንኳን ሳያልፍ መልካም እየስጸፉልዎት አይደል። ለዚያ ነው ከፍ ብዬ ሐቁ የማያውቁት ወይንም መስማት የማይሹት እንዳይሆንብዎ ያልኩት። ዱሮ [ዱሮ ልበል እንጂ] በርስዎ ዘመን ለአዲስ ዓመት በየክፍለ ጦሩ አንዳንድ በሬ ይታረድና ሥጋው ከዛፍ ላይ ከተሰቀለ በኋላ ወታደሩ ኮቸሮውን እየታደለ ከሥጋው ፊት ለፊት ቁጭ ብሎ እንዲበላ ይነገረው ነበር ይባላል። ለምን ቢሉ ለእቁጣጣሽ ሥጋ በላን እንዲል፤ የሚባለውን አጥንት ሰባሪ ቀልድ ከሃያ ዓመት በኋላ አስታወሱኝ።

### *፫ኛ/ መግቢያ*

*"... በአውሮፓ የተካሄዱትን የሶሻሊስት አብዮቶች ፈለግ ለመከተል ካለመቻሉም በላይ ለጊዜው አስፈላጊም ስላልነበረ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ አገሮች የማህበራዊ ለውጥ ሂደት ይበጃል ተብሎ የታመነበትን የአዲሱን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መርህ በመከተል የሶሻሊስት አብዮት ለማካሄድ በእድገት ኋላ ቀርነት ምክንያት የተጓደሉትን ቅድመ ሁኔታዎች በሂደት ለሟሟላት እንዲቻል የተመራ ትግል ነው።"* ደርግ የሕዝብን ትግል መቀማት የጀመረው በሰኔ ፲፱፻፷፮ ሲሆን፤ ጠቅልሎ እጁ ያስገባው በመስከረም ፲፱፻፷፯ ነው። ነገር ግን እርስዎ የሚያወሩለት አዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የታወጀው ከዓመት ከመንፈቅ በኋላ በሚያዝያ ፲፱፻፷፰ ነበርና አይዋሹ። ከዚህ በተጨማሪ በፍጻሜዎ መቃረቢያ ባደረጉልን የኑዛዜ ንግግርዎ፤ ሶሻሊዝምን መርሕ ያደረግነው ፈልገን ሳይሆን ተገድደን ነበር ብለው ያሉንን እንዴት ዘነጉት? እንደ ዕውነቱ ከሆነ፤ ደርግ ሶሻሊዝምን የተቀበለው አውቆትና አምኖበት ሳይሆን ሸብበው ይነዱት በነበሩ መሰርሪዎች እንደነበረ ያደባባይ ምስጢር ነውና ሰሚ አያገኙም።

### *፬ኛ/ የአክሱማውያን መንሥትና ሥልጣኔ አነሳስ*

*"እነዚህ አገሮችና ኃይሎች ከጥንታዊቱ ኢትዮጵያ የኩሻይት፣ የፑንት፣ የዳማትና የአክሱም ስርወ-መንግሥታት ጋር በነበራቸው የንግድ፣ የባሕል፣ የፖለቲካና እንዲሁም የጋራ ደህንነት የመሳሰሉ ብሔራዊ ጥቅማ ጥቅሞች ትብብር፤ ...።"* ኩሽ የነገድ ስም ሲሆን ፑንት ደግሞ የምድር (አገር) ስም ነው፤ ሥርወ መንግሥት በነዚህ ስም የለም።

### *፭ኛ/ ኢትዮጵያ በመካከለኛው ዘመን፡ የአክሱም ዘመን ፍጻሜና የዛጉዌ መንግሥት አነሳስ*

*"ከፈላሻ ሕብረተሰብ የምትወለደዋ ዮዲት ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ፈላሻዎችን፣ የባለቤቷ ወገን የሆኑትን አገዎችንና ሌሎችንም የአክሱማውያንን ሥልጣን ተቀናቃኞች የሆኑ ኃይሎችን ሁሉ አስተባብራ በአክሱም መንግሥት ላይ በመዝመት በቀላሉ ድልን አግኝታ ዘውድ በመቀዳጀት የኢትዮጵያ ንግሥት ለመሆን በቃች።"* በመጀመሪያ ይሁዲት፣ ጉዲት ወይንም እሳቶ በመባል የምትታወቀዋ ስሟ ዮዲት የሚለውን መጠሪያ ያገኘው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው፤ ይሁዲት የሚለውን ለወጥ አድርገውት ነው፤ እነማን፣ ለምን ለሚለው ራሱን የቻለ ሌላ ታሪክ ነው። ጉዲት እንደ ግራኝ መሐመድ የሠራዊቷ መሪ፣ ልክ እንደርስዎ ፈላጭ ቆራጭ ገዢ ነበረች እንጂ በንግሥት ደንብ ዘውድ አልደፋችም፣ ዙፋንም አልነበራትም። እርስዎም ትንሽ ሰንበት ብለው ንጉሥ መንግሥቱ እንዳያስብሉ፤ ሆድ ካንገት በላይ ከሰፈረ ከራርሚልና።

*"... ዛጉዌዎች መጀመሪያ መንግሥታቸውን በሚያቋቁሙበት ጊዜና በኋላ ስልጣናቸውን በተነጠቁበት ጊዜ ከገጠማቸው ችግርና ሁከት በስተቀር የተቀረውን ዘመነ መንግሥታቸውን በሰላም ኖረዋል።"* ዛጌዎች

ሥልጣናቸውን በሰላምና በድርድር እንጂ ተነጥቀው አላስረከቡም፤ ይኽ ቢሆንማ ኖሮ ጃንጥራር የሚባለው ሹመትና ክብር ባልነበረ። በነበራቸው የሐገርና የኃይማኖት ፍቅር፤ ሊከሰት ከነበረው ቀውስ ሥልጣናቸው እንደማይበልጥ በማመን በስምምነት ነው ያስረከቡት። ምን ነበር ቀውሱ የሚል ጠያቂ ካለ ይኽ ቦታው አይደለምና መልሱን በሌላ ጊዜ።

*"ከማንም ሳይወግኑ ኢትዮጵያን ከመስቀል ጦርነት ገለልተኛ ማድረጋቸው የአስተዋይነት እርምጃ ሲሆን፤ ባገኙት ሰላም የሰፈነበት ሦስት መቶ ዓመታት ረጅም ጊዜ በኢኮኖሚ ልማትና በሃገር ግንባታ ረገድ ይህንን ኢደረጉ ተብሎ የሚነገር ነገር የለም።"* ዛጔዎች በሰላም ቢኖሩ ነበርን ዓባይን ለመገደብ ንጉሥ ላሊበላ ሥራ የጀመሩት? ንጉሥ ይምርኻነ ድንቅ ቤተ ክርስቲያንና ቤተ መንግሥታቸውን ሲያንጹ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ከየት ነበር የሚያስመጡት? በተደረጉ ረቂቅ የኢኮኖሚ ግንኙነቶች እንደነበሩ ባስታውስዎስ? እርስዎ በኮርያ መንግሥት ርዳታ ለገተሩት [ትግላችን ሐውልት] ብዙ ሲያውሩ ምነዋ የዛጔዎቹን ድንቅ ዘመን ሊሽራቸው የማይችል ጥበባት ዘነጉት? ከልማት፣ ከግንባታ የማይቆጠር ሆኖ ይሆን? በርስዎ አተረጓጎም ኢኮኖሚ፣ ልማት፣ ግንባታ ምን ማለት ናቸው? ወሬ?

*"... በአባይ ሸለቆና በቀይ ባሕር ጠረፎች በተለይም በዘይላና በታጁራ በሮችና ወደቦች አረቦች ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ ያሻቸውን ሲያደርጉ የገታቸው የለም።"*

*"ከዘመነ አክሱም መጨረሻ ጊዜ ጀምሮ በንግሥት ዮዲትና በዛጉዌዎች ዘመነ መንግሥት ለአራት መቶ ዓመታት ያህል የአረብ ነጋዴዎችና የእስልምና እምነት አስፋፊ መንፈሳዊ የአረብ ምሁራን በፈለጉበት ጊዜ ሲገቡና ሲወጡ በአንድ ሉዓላዊ መንግሥት ሃገር ውስጥ ስለሚያከናውኑት ተግባር ለማወቅና ለመቆጣጠር ቀርቶ ያስተዋላቸውም እንኳን ያለ አይመስልም።"*

*"ስለሆነም ከማዕከላዊ መንግሥት ቁጥጥር ውጪ ከሆኑት የአገሪቱ ሰሜን ምሥራቅ፣ ደቡብ ምሥራቅ፣ ደቡብና ደቡባዊ ምዕራብ ክልሎችና እንዲሁም በመሃል ሸዋ ደቡብና ምዕራብ አውራጃዎች ነዋሪ የሆነው ሕዝብ የእስልምና እምነት ተከታይ በመሆኑ ከአረቡ ዓለም ጋር የደራ ንግድ ባላቸው አሚሮችና ሱልጣናት አመራር ስር የተደራጁ መንግሥታት ተፈጠሩ።"*

በዘይላና ታጁራ ወደቦች የንግድ ልውውጦች ይደረጉ ነበር፤ ነገር ግን በነዚህ ወደቦች የሚገቡና የሚወጡ የእስልምና ተከታይ ነጋዴዎች ንግዳቸው እንዳይሻከርባቸው ሲሉ አልሰበኩም ነበር። በአገሪቱ ላይ የእስላሞች ተጽእኖ መታየት የጀመረው ከአጼ አምደ ጽዮን ጀምሮ ነው፤ በቀይ ባሕር ዳርቻ እስላሞች መስፈር ከጀመሩ በኋላ። እርስዎ እንደሚያስቡት የዚያን ጊዜዎቹ ነገሥታት መደዴ ወይንም በደመ-ነፍስ የሚመሩ አልነበሩም፤ እናም ጥብቅ ቁጥጥር በሚገቡና በሚወጡ ባዕዳን ላይ ይደረግ ነበር። ባይሆን በርስዎ ዘመን ሩሲያውያን ይታሙ ነበር።

ከላይ በጠቀሷቸው ስፍራዎች በዚያ ዘመን የነበረው ሕዝብ እስላም አልነበረም፤ የተፈጠሩም መንግሥታት አልነበሩም።

## *፯ኛ/ ከዛጉዌ በኋላ የመጡ ሥርወ መንግሥታት የጠበቃቸው ሥራና የገጠሟቸው ፈተናዎች*

*"ጥንት በግሪኮችና በሮማውያን ፈረቃ በመጠቃቱ ተዳክሞ የነበረው የቱርክ አጼዎች መንግሥት እንደገና አንሰራርቶ በመነሳት ለዚያን ጊዜ በጣም ዘመናዊ የሆኑ የጦር መሣሪያዎችና መርከቦች ባለቤት በመሆን አውሮፓውያኑን ድል በመምታትና አረቦችን በመተካት በ16ኛው ምዕት ዓመት በቀይ ባሕር፣ በፋርስ ባሕረ ሰላጤ፣ በሕንድ ውቅያኖስና በአካባቢው ብቸኛ ኃያል መንግሥት ሆኖ ብቅ አለ።"* ቱርኮች ከ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት በቦታው ያልነበሩ ናቸው፤ አካባቢውን እንደ ጎርፍ ባጭር ጊዜ ያጥለቀለቁት በዚሁ ክፍለ ዘመን ነው። ታሪክ በይሆናል አይጻፍም፤ ዘንድሮ ደግሞ እንዲህ ዓይነቱን ታሪክ ለማግኘት ከባድ ሆኖ አይመስለኝም።

*"ይኽ በጣም ግልጽ የሆነ አደጋ ምልክት ወይም ማስጠንቀቂያ ሆኖ ሳለ በፖርቹጋል መንግሥት የመመካት ይመስላል አፄ ልብነድንግል በአካባቢው ካሉ የእስላም አገሮች ጋር የነበራቸውን ጤናማ ግንኙነት በማቋረጥ ሁለገብ የስምምነት ውል በመዋዋል በፀረ-እስላም ግምባር ኢትዮጵያ ከፖርቹጋል መንግሥት ጋር ወግና እንድትሰለፍ ተወሰነ።"* ጓድ መንግሥቱ፤ ስለ አጼ ልብነ ድንግል ታሪክ ትንሽ ለማንበብ ሞክረው ቢሆን መልካም ነበር። በታሪክ እንደሚታወቀው ልብነ ድንግል የነገሡት በ፯ ዓመታቸው ነው፤ በዚህ ጊዜ እርሳቸው ጨቅላ ስለነበሩ የመንግሥቱ እንደራሴ እቴጌ ዕሌኒ ነበሩ። በዚያም ዘመን ሆነ ከዚያ ቀደም ባሉት ዘመናት፤ መንግሥት ከእስላሞቹ ጋር የሰላም ስምምነት የሚያደርገው ጉልበቱን ካቀመሰ በኋላ ብቻ እንደነበር ይታወቃል። እናም የነበሩት ጤናማ ግንኙነቶች

ሁሉ ኃይል እስካለ ነበር። ከፖርቱጋሎች ጋር መልካም ግንኙነት የነበረው በእንደራሴይቱ ዘመን ሲሆን፤ አጼ ልብነ ድንግል ራሳቸውን ችለው እንደራሴዋን ገለል ባደረጉ ጊዜ በቤተ መንግሥት አካባቢ ከሚሰልሉት ፖርቱጋሎች ጋር ብዙ ውዝግቦች ተነስተዋል። እንዲያውም ይኸ አለመግባባት ነበር ለግራኝ አመቺ ሁኔታዎችን የፈጠረለት። ግራኝ ከነርሱ ነበር ምሥጢራት እየሾለኩ ይደርሱት የነበረው። ከፖርቱጋልም ጋር የርዳታ ስምምነትን ንጉሡ የጠየቁት የግራኝን ማየል ከተገነዘቡና ምርጫ ስላልነበራቸው ነበር እንጂ ከክርስቲያኖች ጎራ ለመወገን ፈልገው አልነበረም፤ ምክንያቱም በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መኻከል ሊታረቅ የማይችል የዶግማ ልዩነት አለና። እርስዎም አብዮት መራሁ እያሉ ከሚዋሹ፤ ተወርረን ምርጫ ባጣን ጊዜ አገር ለማዳን ስንል ወደ ሶሻሊስቱ ጎራ አዘነበልን ቢሉ ባማረብዎ ነበር።

### *፯ኛ/ ኢማም አህመድ ግራኝ የመራው አመፅ፤ የእስላም አገሮችና የፖርቱጋሎች በኢትዮጵያ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ መግባት*

*"... በኢማም አህመድ ግራኝ በተመራው በእስላማዊ ሠራዊትና በንጉሠ ነገሥቱ ሠራዊት መካከል በሸዋ ክፍለ ሃገር ሽንብራ ኩሬ በተባለ ስፍራ መጋቢት 2 ቀን 1521 ዓ.ም ታላቅ ውጊያ ተደረገ። ..."* ታሪክ የሚያስተምረን ውጊያው የተደረገው በ፲፭፻፳፩ ዓ.ም. እያለ ነው። እርስዎ ግን ይኸ አቆጣጠር በፈረንጆቹ ነው ብለው ስምንቱን ዓመታት ቀነደቧቸው፤ ነገር ግን የኛና የፈረንጆቹ ዘመናት መለያየት የሚጀምሩት ከ፲፭፻፹፫ በኋላ ነው።

*"አፄ ገላውዴዎስ በዚህን ጊዜ በሸዋ ከግራኝ ሠራዊት ኋላ የደፈጣ ውጊያ ይመሩ ስለነበርና ወቅቱም ክረምት በመሆኑ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር መገኛኘት ባይችልም ወጣቱ የፖርቱጋል መኮንን በአካባቢው ከነበሩት ጥቂት የኢትዮጵያ ወታደሮች ጋር ተጠናክሮ በትግራይና በወሎ ሰፍሮ በነበረው የግራኝ ጦር ላይ ሁለት የማጥቃት ውጊያዎችን ሰንዝሮ አመርቂ ድሎችን ለማግኘት ችሎ ነበር።"* አጼ ገላውዲዎስ በዚያ ወቅት በሸዋ አልነበሩም፤ ዛሬ ሰሜን ጎንደር በሚባለው አገር ነው የነበሩት። የፖርቱጋሎች ሠራዊት አጼ ገላውዲዎስ ቆዩኝ እያሉ ቀድሞ ግራኝን የወጋው ድል አድርጎ አሸናፊ መሆኑን ለማሳየትና እርሳቸው ላይ የታቀደውን ተጽእኖ ለማሳደር ነበር። ለኢትዮጵያ ሁሌም ጠበቃ ከላይ አላትና አልተሳካም።

### *፰ኛ/ የኦሮሞ ማህበረሰብ ፈለሳና ወረራ*

ለጊዜው አስተያየት ከመስጠት እቆጠባለሁ።

### *፱ኛ/ የሥርዓተ አልበኞች መሣፍንት ዘመን*

በዚህ ርዕስ ወይንም በቀደመው አሊያም ራሱን የቻለ ምዕራፍ ሊሰጡት የሚገባ ዓቢይ የታሪክ ዘመን አንዲት ዐረፍተ ነገር ነስተውት አልፈዋል። እርሱም የአጼ ሱስንዮስና ከርሳቸው ዘመን ጋር የሚዛመደው ታሪክ ነው። ይኸንን ታሪክ እንዳልነበር ሲያልፉት አንድ ነገር በጭንቅላቴ ደወለ። እርሱም እንዲህ ነው:- ታላቁ የሩሲያ አብዮት እያሉ ሁሌ የሚናገሩለት አብዮት ላይ ነዳጅ ያርከፈከፉ የነበሩት ኃይላት ትዝ ሲሉኝ ነው። ሩሲያን በዚያ ጊዜ ለማድቀቅ የሚፈልጉ ሁለት ኃይላት ነበሩ። ዛር ኒኮላስ [ንጉሡ] በዚያን ወቅት በዓለም አቀፍ ባንኮች ብዙ ሀብት ከማከማቸቱ በተጨማሪ በዓለም የቁማር ገበያ [stock exchange] ላይ ተጽእኖ ማድረግ በመጀመሩ፤ ዓለም አቀፍ ባንኮች ንብረቱን መዝረፍ ይሹ ነበርና እርሱን ማጥፋት ዕቅዳቸው ነበር። ለዚያም ነው አንድም ሰው ከቤተሰቡ እንዳይተርፍ አድርገው የረሸኗቸው፤ ወራሽ እንዳይገኝ።

ሁለተኛው ኃይል ደግሞ የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ናት። የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በኃይል ተገድዳ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንን ላታወግዝና አብራ በሕብረት ልትሠራ ስትስማማ፤ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ሳትስማማ ቀርታለች። የሩሲያ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ደግሞ ንጉሡ በመሆኑ፤ በእምቢተኝነቱ ምክንያት ይዘግይ እንጂ የሮማ ቤተ ክርስቲያንን ክንድ መቅመሱ አይቀሬ ነበር፤ ቀመሰ። ይኸ ረጅምና ጨካኝ እጅ [የሮማ ካቶሊክ] ከርስዎም በስተ ጀርባ እንደነበር ብዙ ፍንጮች አሉ። አሁን ደግሞ ስለርሱ እንደማያውቅ በጎን ሲያልፉ፤ ዕውነትም ነበረ ለማለት አስደፈረኝ። ከርስዎ በላይ ጨካኝ እንደሆነ ያውቁት የለ!!!

*"በዚህ ጊዜ ነበር ጎንደር ውስጥ ደንቢያ ከምትባል ወረዳ ውስጥ ከምትገኝ ቋራ ከምትባል ስፍራ ከተራ ገበሬ ቤተሰብ የሚወለድ ካሳ ኃይሉ የሚባል ሰው ወደ ትግሉ መድረክ ብቅ ያለው። ..."* ፲፯ ዓመት የገዟትን አገርዎን እንኳን በቅጡ አያውቋትም፤ አንድ ሰውና አንድ ጥይት እያሉ ራስዎን

የሚመስስሉባቸውን የቴዎድሮስን ታሪክ እንኳ ምነው በሚገባ ቢያነቡ። ደንቢያና ቋራ በምንም የማይገናኙ ናቸው፤ ቋራ ደሞ ስፍራ ሳይሆን በደጃዝማች ይተዳደር የነበር ግዛት ነው።

ካሣ የሚወለዱት ከገበሬ ቤተሰብ አይደለም፤ አባታቸው ደጃዝማች ኃይሉ በቀጥታ ከአጼ ፋሲል የዘር ሐረግ አላቸው። እናታቸው አትጠገብ ደግሞ፤ አባታቸው ደጃዝማች ወንድወሰን ሲሆኑ እናታቸው ወይዘሮ ትሳል ከነገሥታት ዘር የሚወለዱ ናቸው። ኢትዮጵያ አጼ ቴዎድሮስ የገበሬ ልጅ ቢሆኑ አታፍርባቸውም፤ ምክንያቱም የገረድ ልጅ ምኒልክን ያነገሠች ሐገር ናትና። የሚያሳፍረው ሐሰትን ዕውነት ብሎ መናገር ነው።

*“ክሮምዌል በነቃ የእንግሊዝ ሕዝብ መካከል በመወለዱ በወገኖቹ ብቻ ሳይሆን በዓለም ሕዝብ ዘንድ ሲመሰገንና ሲወደስበት ኢትዮጵያዊው ቴዎድሮስ በኋላ ቀር ሕዝብ መካከል ያለጊዜያቸው ተወልደው ለሃገርና ለወገን ብለው የሰሩት ሥራ ሕይወትን ያህል ነገር ለሚያስከፍል መስዋዕትነት ዳረጋቸው።”* ጓድ ሊቀመንበር፤ ስለማያውቁት ታሪክ ለምን ይናገራሉ። ክሮምዌል በእንግሊዝ ታሪክ ጸሐፍት ዘንድ ውጉዝ ከመ አርዮስ እንደሚባል ብናገር በተገኘበት ይገደል እንደማይሉኝ አምናለሁ። ባይሆን ስለሸመደዱት ስለ ሩሲያ አብዮት ቢያወጉ የለመድነው ነውና አንደነቅም። አጼ ቴዎድሮስ ሕይወት ከመክፈላቸው በፊት አልረገሙንም፣ ባይሆን ወቅሰውን ይሆናል፤ እናም በደስታና በክብር ነው ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡልን። *ምናልባት በዚያ ዘመን አውሮፕላን ቢኖር ... ለማለት እንዳይሚከሩ፤ ወንድ አጄን ጨብጦት አያውቅም* የሚለው ደብዳቤያቸውን እማኝ እጠራብዎታለሁ።

*“የቴዎድሮስን ዓላማ፣ የቴዎድሮስን ማንነትና በኋላም በአጭሩ የተቀጨበትን ምክንያት የተጋደሉለት የእሳቸው ትውልድ ቀርቶ የዛሬውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቀዋል ለማለት አያስደፈርም።...”* አጼ ቴዎድሮስ በታሪክ የሚከሰሱባቸው አእላፍ ጥፋቶች አሏቸው፤ ይሁንም እንጂ ያንን ሁሉ ጥፋት በደማቸው አጥበውታልና ወቃሽ የላቸውም። በርሳቸው ዘመንማ፤ *አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ* ...፤ ያስባሉ ጨካኝ እንደነበሩ የዚያን ዘመን ኗሪዎች ትተውልን አልፈዋል። ስለ ታሪክ ደግሞ የነበረ እንጂ ለኛ በቃልና በጽሑፍ የሚነግረን፤ እንደርስዎ በመላ ምት ከዘመናት በኋላ የሚደናበር አይደለም። ምናልባት ስለኔ ወደፊት ጥሩ መነገር ይገባዋል የሚሉ ከሆነ፤ እርሱ የኛና የልጆቻችን ጉዳይ እንጂ የርስዎ አይደለምና በከንቱ አይድከሙ።

*“አፄ ቴዎድሮስ የታገሉለት የራሳቸው ትውልድ ለወራሪው የእንግሊዝ ሠራዊት ቀለብና ፍሪዳ እያቀረበ፣ መንገድ እየሰራና እስከ መቅደላ አጅቦ ከማምጣት ባሻገር የመቅደላን ምሽግ ዙሪያ ከብቦ ቴዎድሮስንና ሠራዊታቸውን መፈናፈኛ በማሳጣት ያንን መሪር ውሳኔ እንዲወስኑ አስገድዷቸው በራሳቸው ላይ ሲፈርዱ አፅማቸውን ባይሆን ስማቸውን ከትቢያ አውጥቶ ተገቢውን ክብር ሊሰጣቸውና ሊያሞካሻቸው የሞከረው የእኛ አባቶችና የእኛ ትውልድ ነው።”* ሕዝብ የጎዳውንና ያቆሰለውን በተለያየ መንገድ ይበቀላል፤ ቴዎድሮስ ሕዝብን በድለው ስለነበር ሸሻቸው። ልክ እርስዎን እንደሸሸ። ሕዝብ ዐዋቂ ባይሆን ነው ምኒልክን ትከትሎ እስከ አድዋ የዘመተው? የነገርዎ ዳር ዳር ግልጽ ነው፤ ራስዎን በቴዎድሮስ ለማስታከክ። የአጼ ቴዎድሮስ ታሪክ በክፉም በደግም ይነሣ ነበረ፤ *ገደልን እንዳይሉ* ...፤ *አርብ አርብ ይሸበራል* ...፤ ያለላቸው እኮ እርሳቸው የነበሩበት ትውልድ ነው። ደግሞም የእርስዎ አባቶች ታሪካቸውን በደግ ከዘገቡላቸው፤ አያትዎ የቴዎድሮስ ዘመን ሰው ናቸውና ምኑ ነው ጥፋቱ?